
# እ.ኤ.አ ከማርች 21-31/2018 የነበረው
# የአየር ሁኔታ ግምገማ

በማርች ሶስተኛው አሥር ቀናት በደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ተወስኖ የነበረዉ የዝናብ መጠን እና ስርጭት ቀስ በቀስ በመጨረሻዎቹ ጥቂት ቀናት ዝናቡ ወደ ምዕራብ እና ደቡብ ምዕራብ ክፍሎች ላይ ተስፋፍቶ ተስተዉሏል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከተጠናከሩ የደመና ክምችት በጥቂት ስፍራዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸው ስፍራዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በማጂ 54.3፣ በበደሌ 39.2፣ በነገሌ ቦረና 35.8 እና በጨራ 30.0 በሚ.ሜ. ይገኙበታል፡፡


በአሥሩ ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ከ25-113 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ በቤንች ማጂ፣ ጋሞጎፋ፣ በደቡብ ኦሞ፣ በከፋ፣ በሸካ፣ በጋምቤላ ዞኖች፣ በቄለም ወለጋ፣ በምዕራብ ወለጋ፣ በኢሉአባቦራ፣ በጂማ፣ በአሶሳ፣ በከማሽ፣ በጉጂ፣ ቦረና እና ባሌ ዞኖች ላይ ከ5-8 ቀናት የተመዘገበ ሲሆን በወላይታ፣ በሀዲያ፣ በጉራጌ፣ በሊበን፣ በአርሲ፣ ምዕራብ ሸዋ፣ በምዕራብ ሀረርጌ፣ በመተከል፣ በምዕራብ ጎጃም እና በሰሜን ጎንደር ዞኖች ላይም ከ5-38 ከ2-4 ቀናት ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ሳሳ ያለ የደመና ሽፋን እየተስተዋለባቸዉ በአመዛኙ ደረቅ ሆነው ሰንብተዋል (ካርታ 1 እና 2)።

በአሥሩ ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር የሰሜን ጎንደር፣ ምዕራብ ጎጃም፣ ሁሉም የቤኒሻንጉል-ጉሙዝ እና ጋምቤላ ክልል ዞኖች፣ ምዕራብ፣ ቄለም እና ምስራቅ ወለጋ እንዲሁም ጥቂት ቤንች ማጂ ዞኖችን ጨምሮ ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ ነበራቸዉ፡፡ በተጨማሪም የደቡብ ኦሞ፣ ከፋ እና ሸካ፣ ቦረና፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ጎዴ፣ አፍዴር እና ቆራሂ ዞኖች በአብዛኛዉ ከመደበኛዉ ጋር የተቀራረበ ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች ከመደበኛ በታች የሆነ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 3)።


## ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከማርች 21-31/2018 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



## ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከማርች 21-31/2018 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት ብዛት



ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2018 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር





ከመደበኛ በታች    መደበኛ    ከመደበኛ በላይ

# <u>እ.ኤ.አ ከማርች 21- 31/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ</u>

በማርች ሶስተኛዉ አሥር ቀናት በደቡብ እና ደቡብ ምእራብ የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ ጥሩ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው ፡፡ ይህም የተገኘው እርጥበት ለበልግ ተጠቃሚ አካባቢዎች በተለያየ የእድገት ደረጃ ለሚገኙ ሰብሎች፣ የበልግን እርሻ ስራ እንቅስቃሴ ዘግይተው ለሚያካሂዱ እና የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለሚጠቀሙ አካባቢዎች ለማሣ ዝግጅትና ለዘር ጊዜ አመቺ ሁኔታ የፈጠረ ነበር፡፡ በተጨማሪም ከላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች የተገኘዉ እርጥበት ለቋሚ ተክሎች የዉሃ ፍላጎት መሟላት እና ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለመጠጥ ውሀና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት የጎላ ጠቀሜታ ነበረው። በሌላ በኩል በመካከለኛዉ እና በሰሜን ምስራቅ በልግ አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች የነበረው ደረቅ ሁኔታ ለበልግ የግብርና ስራ እንቅስቃሴ አሉታዊ ተጽእኖ ነበረዉ (ካርታ 4)፡፡

**ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2018 ድረስ የነበረዉ የዕርጥበት ሁኔታ**




## እ.ኤ.አ ከማርች 21-31/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ

## በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደርው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 21-31 ማርች 2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ የነበራቸው የመካከለኛው ገናሌዳዋ፣ አብዛኛው ባሮአኮቦና የመካከለኛው ኦሞጊቤ አዋሳኝ ከፍተኛ ቦታዎች እና የታችኛው ስምጥሸለቆ ተፋሰሶች ናቸው። በሌላ በኩል መጠነኛ እርጥበት የነበራቸው ተፋሰሶች የላይኛውና የታችኛው ገናሌዳዋና የመካከለኛው ተከዜ፣ አባይ ኪስ ቦታዎች ናቸው። በሌላ በኩል መጠነኛ እርጥበት የነበራቸው ተፋሰሶች ደግሞ ጥቂት የደቡባዊና ምስራቃዊ አባይ፣ የመካከለኛውና የታችኛው ኦሞጊቤ፣ የላይኛው ባሮአኮቦ፣ የታችኛው ስምጥሸለቆ፣ አብዛኛው አዋሽ፣ የላይኛው ገናሌዳዋና የመካከለኛው ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች ናቸው። የተቀሩት አብዛኛው ተከዜ፣ የአባይ ምእራባዊ አጋማሽ፣ አጋዴን፣ የታችኛው ባሮአኮቦና የታችኛው ዋቢሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ ተስተውሏል (ካርታ 5)።

**ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከማርች 21 እስከ 31/2018 ድረስ የነበረዉ የዕርጥበት ሁኔታ**



## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-10/2018 የሚኖረው

## የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በአፕሪል የመጀመሪያው አሥር ቀናት ከቀዳሚው አሥር ቀናት በተሻለ መልኩ የበልግ ዝናብ በአብዛኛዎቹ የበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ እየተጠናከረና እየተስፋፋ የሚሄድበት ጊዜ ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞም ወቅታዊው ዝናብ በተለይም በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ ክፍሎች ላይ እንደሚስፋፋ ይጠበቃል።

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በተለይም በበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ሥፍራዎች ላይ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለያዩ ቀናት አንጻራዊ ጥንካሬ ሊያሳዩ እንደሚችሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በአጠቃላይ ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ እና ምእራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ ምዕራብና ሰሜን ሸዋ፣ አዲስ አበባ፤ የምዕራብና የምሥራቅ ሐረርጌ፤ አርሲና ቦሌ፣ ቦረናና ጉጂ፤ የሀረሪና የድሬዳዋ፤ አንዳንድ የጋምቤላ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ፣የባህር ዳር ዙሪያ፣ደቡብ ጎንደር እንዲሁም ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም፤ ከአፋር ዞን 3 እና 5፤ ከትግራይ ክልል የመካከለኛው፣ የምሥራቅና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ሁሉም የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልልና አብዛኛው የሶማሌ ዞኖች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል።በተጨማሪም ከሚጠናከሩ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ አልፎ አልፎ ከባድ ዝናብ ይኖራል። የዝናብ መጠኑም ብዙውን ጊዜ ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ሊሆን ይችላል። የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በአመዛኙ ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1-10/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ በአፕሪል ወር የመጀመሪዎቹ አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ ዝናቡ የሚስፋፋበትና በአንፃራዊነት የተሻለ እርጥበት የሚገኝበት ወቅት ነው፡፡ በመሆኑም ከግብርና እንቅስቃሴ አኳያም በበልግ ወቅት መጀመሪያ ወራት ላይ አስቀድመው የተዘሩ የተለያዩ ሰብሎች በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ የሚደርሱበት ጊዜ ነው፡፡ በሌላም በኩል የረጅም ጊዜ ሰብል አምራች የሆኑ አካባቢዎች እንደ በቆሎና ማሽላ የመሳሰሉትን የመኽር ሰብሎች ለመዝራት ዝግጅት የሚያደርጉበትና የሚዘሩበት ወቅት እንደሆነ ይታወቃል፡፡

በሚቀጥለዉ የአፕሪል ወር የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት የዝናቡ ሁኔታ በመጠንም ይሁን በስርጭት በተለይም የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የተሻለ እንደሚሆን በተሰጠው

የአየር ሁኔታ ትንበያ ላይ ተመልክቷል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በተለያዩ የኦሮሚያ፣ የአማራ፣ የጋምቤላ፣ የሀረሪ፣ የድሬዳዋ፣ የትግራይና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ህዝቦች ክልል ውስጥ በሚገኙ አንዳንድ የበልግ ሰብል አብቃይ እና የአርብቶ አደር አካባቢ ዞኖች የተለያየ መጠን ያለው ዝናብ ሊያገኙ እንደሚችሉ በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ ውስጥ ተገልፅዋል፡፡ ይህም ሁኔታ ከግብርና እንቅስቃሴ አንፃር ዘርፉ ብዙ ጥቅም እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡ አስቀድመው ተዘርተው በአሁኑ ወቅት በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች የውኃ ፍላጎታቸውን ከሟሟላት አንፃር የሚኖረው ሚና ከፍተኛ እንደሚሆን በተለይም ባሳለፍናቸው አስር ቀናት በነበሩት ተከታታይ ደረቅ ሰሞናት ጋር ተያይዞ የተፈጠረውን የእርጥበት እጥረት እንደሚያረግብ ይጠበቃል፡፡

ከዚያም አልፎ ከአፕሪል ጀምሮ ለሚዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ የመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎችን ለመዝራት ምቹ አጋጣሚ ሊኖር እንደሚችል ይታመናል፡፡ ለአርብቶ አደርና ከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚጠበቀው እርጥበት የግጦሽ ሳርንና ሌሎች መኖዎችን ለማቅረብም ሆነ የመጠጥ ውኃ አቅርቦትን ከማሻሻልም አልፎ የተለያዩ ሰው ሰራሽም ሆኑ የተፈጥሮ ምንጮችን ከማጎልበት አንፃር አዎንታዊ አስተዋፅዖ ይኖረዋል፡፡ በሌላ መልኩ በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችልበት አጋጣሚ ሊኖር ስለሚችል በተለይም ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎች ጥንቃቄ ሊያደርጉ ያስፈልጋል፡፡ ሆኖም በተለይም ዝናብ አጠር የሆኑ አካባቢዎች የሚያገኙትን ውኃ ለመያዝና በማሳ ላይ ለማቆየት የሚያስችሉ ተግባራትን ከማከናወን ጋር የሚፈጠሩ የጎርፎ ውኃዎችን ወደ ሰብል ማሳዎችም ሆነ ወደ ውሃ ማጠራቀሚያ ኩሬዎች እንዲገቡ ማድረግ ጠቀሜታው የጎላ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡

## እ. ኤ. አ ከኤፕሪል 1-10/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በተሰጠው ትንበያ መሰረት በሚቀጥሉት አስር ቀናት የበልግ ዝናብ በአብዛኛዎቹ የአገሪቱ ተፋሰሶች ለይ እየተስፋፋ እንደሚሄድ እና የተሻለ እርጥበት እንደሚኖር ይጠበቃል። በዚህ መሰረት አብዛኛው ባሮአኮቦ፣ የታችኛው አባይ፣ ገናሌዳዋ፣ ኦሞጊቤና ስምጥሸለቆ፣ የታችኛውና የመካከለኛው ተከዜ እንዲሁም የታችኛው አዋሽ ተፋሰሶች በአብዛኛው መደበኛና ጥቂት ቦታዎች ደግሞ ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ እንደሚያገኙ ተጠቁሟል። በተጨማሪም የላይኛውና የመካከለኛው ዋቢሸበሌ፣ መካከለኛው አዋሽ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ገናሌዳዋ እና የላይኛው ተከዜ ደቡባዊ ክፍል ተፋሰሶች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። ይህም ሁኔታ በብዙዎቹ ተፋሰሶች ላይ የሚኖረው የደመና ሽፋንና የዝናብ መኖር በዚህ

ወር የሚኖረውን ሙቀት በመቀነስ በውሃ አካላት ላይ የሚኖረውን የትነት መጠን እንዲቀንስ አስተዋፆ ከማድረጉም በላይ የውሃ እጥረት ለሚታይባቸው ተፋሰሶች በትንንሽ ወንዞች ውስጥ ውሃ እንዲኖራቸው አስተዋፆ ያደርጋል።